
Y
Ethio
QUESTHION
JOIN OUR CHANAL:-
@all_question

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
# የ ስምንተኛ ክፍል የሥነ-ዜጋና ሥነምግባር ሞዴል ፈተና
# 2012/2020

**የጥያቄዎች ብዛት: 60** **የተሰጠውጊዜ: 60ደቂቃ**

1. ከሚከተሉት መሰከል የዲሞክራሲያዊ መንግስት መገለጫ የሆነው የቱ ነው?

   A. ስልጣን በአንድ ሰው እጅ ስር መግባት
   B. ህዝቦች የስልጣን ምንጭ መሆናቸው
   C. የመንግስት ስልጣን ያልተገደበ መሆን
   D. ዜጎች የሚፈልጉትን ካለገደብ ማድረግ

2. በአንድ ሀገር ውስጥ መቻቻል መኖሩን የሚገልፀው ወረፍተነገር የቱ ነው?

   A. በመከባበርና በአብሮነት መኖር መቻል።
   B. ከሰላም በፊት ለእድገት ትኩረት መስጠት።
   C. የራስ እመሰካከትን በሰዎች ላይ መጫን።
   D. ለሰላም ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆን።

3. ከሚከተሉት ውስጥ በኢትዮጲያ የብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ተግባር የሆነው የትኛው ነው?

   A. አለም አተፍ ስምምነቶችን ማፅደቅ።
   B. የውጭ ግንኙነቶች በተመለከተ መወሰን።
   C. የክልሉን ህገመንግስት ማውጣጥ።
   D. የፌደራል ህገመንግስትን ማፅደቅ።

# 2 2 2

4. የኢትዮጲያ ሰላም አስከባሪ ሰራዊት በአፍሪካ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ በየትኛው ሃገር ተሰማርቶ ነበር?

A. ሲቢያ
B. ዩጋንዳ
C. ደቡብ አፍሪካ
D. ኮንጎ

5. ከተማሪዎች የሚጠበቅ ሥነ-ምግባር የቱ ነው?

A. በትምህርት ቤት የአምነት አመለካከትን ማራመድ
B. የጓደኞቻቸውን ሚስጥር ማውጣት
C የጋራ መገልገያ ቁሳቁሶችን መንከባከብ
D የሚሰጣቸውን የቤት ስራ ጓደኞቻቸው እንዲሰሩት መተው

6. ከሚከተሉት መካከል የህግ የበላይነት ተግባራዊ የሚሆነው በየትኛው የመንግስት ሥርዓት ነው?

A. በአንባገነናዊ መንግስት
B. በዘውዳዊ መንግስት
C በኃይማኖታዊ መንግስት
D. ድሞክራሲያዊ መንግስት

7. ከሚከተሉት መካከል ለሙስና መስፋፋት ምክንያት የሚሆነው የቱ ነው?

A. የራስ ወዳድነት መኖር
B. የቴክኖሎጅ እድገት
C. የኢኮኖሚ ውድቀት
D. የግጭት መስፋፋት

8. የአካል ጉዳተኞችን መብት ማክበር የሚኖረው ጥቅም ምንድን ነው?

A. የተጎጂዎችን ቁጥር ይጨምራል
B. የዝቂ ምንጫቸው ይጨምራል
C. ያላቸውን አቅም ለመጠቀም ያስችላል
D. ጥገኝነት እንዲስፋፋ ያደርጋል

2 3 2

9. በኢፌዲሪ ሕገመንግስት መሠረት የቋንቋ እኩልነት መከበር ምን ጠቀሜታ ያስገኛል?

A. በፈደራል የሥራ ቋንቋ መግባት ያስችላል።
B. ቋንቋቸው ከሌሎች የበላይ እንዲሆን ያደርጋል።
C. ቋንቋቸውንና ታሪክቸው እዲያሳድጉ ለማስቻል።
D. የሌሎችን ባህልና ወግ እንዲወርሱ ያደርጋል።

10. ከአድልኦ የፀዳ አሰራር ማለት ምን ማለት ነው?

A. በእኩል ያለ አድሎ በትንነት ማገልገል ማለት ነው።
B. ኃላፊዎች ቅድሚያ ለቤተሰቦቻቸው መስጠት።
C. የአገልግሎት ጊዜን ለማሳጠር የማገዛያ ድርጊቶችን መፈፀም።
D. ሀላፊዎች ለሰጡት አገልግሎት ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ ማለትነው።

11. በማሕበረሰቡ አባላት መካከል ግጭት ሲከሰት ግጭቱን ለመፍታት የሚያስችለው የፍትህ ተቋማት የትኛው ነው?

A. የፖለቲካ ፓርቲዎች
B. ፍርድ ቤቶች
C. የሚኒስሮች ምክር ቤት
D. የህገዛ ተወካዮች ምክር ቤት

12. በኢትዮጲያ ተዛብተው የተፃፉ ታሪክችን የምናስተካክልበት መንገድ የትኛው ነው?

A. ቀድሞ የተሰሩትን ታሪክች ማጥላላት
B. ቀደምት ታሪክችን በማጋነን እንደገና መጻፍ
C. አሁን ላሉ መሪዎች ተጠቂ ያልሆነ ክብር መስጠት
D. ስህተቱን በማረም ትክክለኛውን ታሪክ መፃፍ

2 4 2

13. አሁን ያለው የኢትዮጲያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት አቀማመጥ ከታች ወደላይ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ
B. ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ
C. ቢጫ፣ቀይ፣ አረንጓዴ
D. አረንጓዴ፣ቀይ፣ ቢጫ

14. ከሚከተሉት ውስጥ ቃልኪዳን የሚለውን ቃል የሚገልፀው ትርጉም የትኛው ነው? ቃልኪዳን÷

A. ግላዊ ጥቅምን ለማስከበር በጥንካሬ ሰርቶ ማግኘት።
B. በተሰማሩበት የሥራ መስክ ኑሮን ለማሸነፍ ተግቶ መስራት።
C. የሰዎችን ስብእናና ክብር ላይነኩ የግል ሥራን መስራት።
D. የተሰጠን ኃላፊነት መወጣትና አደራን ማክበር።

15. ታሪካዊ ቅርሶችን ለመንከባከብ ከዜጎች የሚጠበቀው ግዴታ ምንድን ነው?

A. ኃላፊነቱ የመንግስት መሆኑን አውቆ ጣልቃ አለመግባት
B. የጋር ሃላፊነት መሆኑን ተገንዝበው ተገቢውን ጥበቃ ማደረግ
C. ቅርሶችን ለሀገር በሚጠቅም መልኩ ለሽያጭ ማቅረብ
D. የፈራረሱ ቅርሶችን ይዘታቸውን ቀይሮ በዘመናዊ መልክ መስራት

16. ከሚከተሉት ውስጥ እንዱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከት ትክክል ነው?

A. ዘርና ሐይማኖትን ለይቶ ያጠቃል።
B. በበሽታው ካለባቸው ሰዎች በመራቅ ራስን መከላከል።
C. በሀገርና በግለሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል።
D. በንክኪ ከሰው ወደ ሰው መተላለፍ።

2 5 2

17. "ሁሉም ኢትዮጲያዊ መተዳደሪያውን እና መሥራት የመምረጥ መብት አለው።" ይህ የህገመንግስት ድንጋጌ ከትኛው የመብት ዓይነት ይመደባል?

A. በባህላዊ
B. በማህበራዊ
C. በፖለቲካ
D. በኢኮኖሚያዊ

18. በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ ያለ ሰው በአቅሙ መስራት የሚችለውን እና ለራሱ የሚየያስፈልጉትን ነገሮች ሌሎች እንዲሰሩለት መፈለግምን ይባላል?

A. ራስን መቻል
B. የበላይነት ስሜት
C. የጥገኝነት ስሜት
D. በራስ መተማመን

19. የውጤታማ ሰው መገለጫ የሆነው የቱ ነው?

A. በራሱ ተነሳሽነት ስራዎችን በአግባቡ የሚሰራ ነው።
B. በሁሉም መሥያዎች የመጀመሪያና ከዚያ በላይ ድግሪ ያለው ነው።
C. በህጋዊም ሆነ በህገወጥ መንገድ ኃብታም የሆነ ።
D. በራሱ የሚመራ ነገር ግን ከሌሎች መማር ዝግጁ ያልሆነ።

20. ከሚከተሉት መነሻል ስለቁጠባ ትክክል የሆነውን ለዩ›

A. ባህላዊ የቁጠባ ዘዴ የቁጠባ ባህልን ለማሳደግ አስተዋፅኦ የለውም።
B. ያለዘመናዊ የቁጠባ ተቋም መቆጠብ አይቻልም።
C. ለምች የሚቆጥቡት በለምች ዘንድ ክብር ለማግኘት ነው።
D. ዜጎች ህይወታቸውን በትክክል ለመምራት ያግዛቸዋል።

21. የቁጠባ ባህል መዳበር አስፈላጊነቱ ምንድን ነው?

A. ከፍተኛ በሆነ ወጭ ሰርግ ለማስረግ
B. የብድር ምንጮችን ለማስፋት
C. የተረጋጋና ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር
D. በዜጎች መነሻል ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ለመፍጠር

2 6 2

22. ሰዎች በአቅድ እንዲመሩ የሚያደርጋቸው ምክንያት ምንድን ነው?

A. በኢኮኖሚ ያደጉ መሆናቸው
B. በአቅም ልክ ለመኖር
C. ዘመናዊ የአኗኗር ዘዴ የሚከተሉ መሆናቸው
D. የከተማ ነዋሪ መሆናቸው

23. መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም በተለያዩ በጎፍቃደኞች የሚቋቋም ድርጅት ምን ይባላል?

A. የፖለቲካ ፓርቲ
B. የጎይማኖት ተቋማት
C. የአክሲዮን ማህበር
D. የሲቪክ ማህበራት

24. ስለ መረጃ ትክክል የሆነው ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A. ሰዎች በተፈጥሮ የሚኖራቸው መንፈሳዊ ሃብት ነው
B. እውቀት የማግኛና ማስፋፊያ ዘዴ ነው
C. መሰረታዊ የድሞክራሲ መርህ ነው
D. አፍራሽ ልምዶች እንዲስፋፉ የሚድረጊያ ዘዴ ነው።

25. ከሚከተሉት መሰክል የንበብ ጥቅም የሆነው የትኛው ነው?

A. ሰዎችን በዕውቀት ላይ የተንሳፃ መልካም ባህሪ ማላበስ።
B. ሰዎች ክፉም ሆን ደግ ያነበቡትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማገዝ።
C. ዜጎች ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ደረጃ እንዲኖራቸው የስችላል።
D. በዜጎች ተመሳሳይ አመለካከት እንድኖራቸው ያግዛል።

2 7 2

26. ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት መከተል የሚገባቸው የንባብ ዘዴ የትኛው ነው?

A. ቃላቶችን ነጥሎ ማንበብ
B. ሁሉንም በቃል ለመያዝ ማንበብ
C. በፍጥነት በገረፍ ገረፍ ማንበብ
D. ደረጃ በደረጃ በጥልቀት ማንበብ

27. ከሚከተሉት የድሞክራሲ መርሆች መከክል ኃላፊዎች የሚያከናውኑትን ተግባር ለህዝቡ ማሳወቅ እንዳለባቸው የሚያስገድደው መርህ የቱ ነው?

A. ተጠያቂነት
B. ግልፀኝነት
C. ፍታሃዊነት
D. ታማኝነት

28. ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከሰብአዊ መብቶች በምን ይለያሉ?

A. በተፈጥሮ የምናኛቸው መብቶች ናቸው።
B. ለአደጉ ሀገራት ብቻ የተፈቀዱ መብቶች ናቸው።
C. በዲሞክራሲያዊ ስራዓት የሚገኙ መብቶች ናቸው።
D. ለህፃናትና ለጎልማሶች የሚሰጡ መብቶች ናቸው።

29. ከሚከተሉት መከክል ስለ ፌደራልና የክልል መንግሥታት ዐወቃቀር ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. ሁለቱም የፌደራሉን ህገመንግስት በጋራ የመጠበቅ ግደታ አለባቸው።
B. ሁለቱም ተመሳሳይ የስልጣን አወቃቀር የላቸውም።
C. የፌዴራል መንግስት በኩታማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው።
D. ክልሎች የፌዴሬሽን ምክር ቤት በማዋቀር ተግባራቸውን ያከናውናሉ

2 8 2

30. የኢትዮጲያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አላማ የሆነው የቱ ነው?

A. ግዙፍ ወታደራዊ ኃይል ማደራጀት።
B. ድሞክራሲያዊ ስራዓትን ማጠናከር።
C. ሌሎች ሀገራት ላይ ፖለቲካዊ ተፅኖ ማድረግ።
D. ጎረቤት ሃገሮች አብሮታዊ ድሞክራሲን እንዲተክሉ ማድረግ።

31. የክልል ህገመንግስትን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እገልግሎት ይሰጣል።
B. የፌደራል ህገመንግሥትን የሚቃረን ነው።
C. በፈደራል ምክር ቤት የፀደቀ ህገመንግስት ነው።
D. በክልል ደረጃ የሚተገበሩ ህጎች የበላይ ህግ ነው።

32. ሚስጥርን በተጠቂው ሁኔታ ለመጠበቅ ከሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች መካከል ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. የመንግስትን ጉድለቶች በጥንቃቄ መያዝ
B. ወታደራዊ የሆኑ ሚስጥሮችን በጥንቃቄ መያዝ
C. ሚስጥራዊ ፋይሎችን ለድፕሎማቶች ብቻ ማሳወቅ
D. ዜጎች የሃገራቸውን ሚስጥር እንዲያውቁ ማድረግ

33. ሙስናን ለመከላከል ኃላፊነት የተሰጠው የፍትህ ተቋማት የቱ ነው?

A. የሲቪክ ማህበር C. አቃቤ ህግ
B. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት D. የሙያ ማህበር

34. ለዜሐር፡ዜሐረሰቦች አካባቢያቸውን የማስተዳደር መብት መሰጠቱ የሚኖረው ጥቅም ምንድን ነው?

A. የራስን ዕድል በራስ ለመወሰን
B. ስልጣን ለሁሉም ለማዳረስ
C. አመራሮችን ባለፀጋ ለማድረግ
D. የሌሎችን ሰላም ለማወክ

35. ሁሉም ዜጎች በሀገራቸው እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችለው የትኛው ነው?

A. የመንግስት መሰረያ ቤት ቁጥርን መጨመር
B. የመልካም አስተዳደር መጓደል
C. የህዝብ ተወካዮችን ቁጥር መጨመር
D. ዲሞክራሲያዊ ሥራዉትን መዘርጋት

36. "ያለሴቶች ተሳትፎ የሚካሄድ የልማት እንቅስቃሴ በአንድ እጅ እንደ ማጨብጨብ ነው።" ይህን አባባል በትክክል የሚገልፀው የቱ ነው?

A. ሴቶች በብዙኀነት ልማትን መምራት አለባቸው ማለት ነው።
B. ሴቶችን ያሳተፈ የልማት እንቅስቃሴ የተሟላ አይደለም
C. ያለሴቶች ተሳትፎ ልማትን ማረጋገጥ ይቻላል ማለት ነው።
D. ሴቶች በልማት ያላቸው ሚና የጎላ አይደለም ማለት ነው።

**37.** በአንድ ሀገር ውስጥ ፍትህ መጓደል ውጤት የሆነው የትኛው ነው?

A. የባዕድ ባህሎች መስፋፋት
B. የዜጎች አመለካከት መለያየት
C. ሀገራዊ አንዲነት መላላት
D. የዜጎች የኢኮኖሚ ደረጃ መለያየት

38. ትክክለኛ የዳኝነት ስርዓት እንዲኖር የዜጎች ሚና ምንድን ነው?

A. ዜጎች ህግን በማወቅ ለተግባራዊነቱ መታገል።
B. ሁበረተሰቡ በአካባቢው በጋራ እንዲዳኝ ማድረግ።
C. ለፍትህ አካላት የገንዘብ ጉርሻ መስጠት።
D. ዜጎች መብታቸውን በማንኛውም መንገድ ማስከበር።

2 10 2

39. ከሚከተሉት መከከል በክልል ደረጃ ጊዜያዊ አዋጅን የማፅደቅ ስልጣል ያለው ማን ነው?

A. የፌደራሽን ምክር ቤት
B. የክልል ምክር ቤት
C. የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት
D. የክልሉ ፍርድቤት

40. የህዝብን ሰላምና ደህንነት ከስጋት ለመጠበቅ ኩተማሪዎች ምን ይጠበቃል?

A. ሰላምን የሚያውኩ ሰዎች ሲያጋጥሙ ቢጎይል ማስቆም
B. በጥፋት ኩተሰማሩት ቡድኖችጋር በመተባበር ችግሩን መፍታት
C. አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸውን ግለሰቦች ለሚመለከተው አካላት ማሳወቅ
D. የአካባቢያቸውን ሰላምና ደህንነት በመደራጀት ቢጎይል መመከት

41. ድህነትን ለማስወገድ ከመንግስት የሚጠበቀው ተግባር የትኛው ነው?

A. እርዳታ በማምጣት ለዜጎች ማከፋፈል
B. ለዜጎች በአመራር ሙያ የውጭ ትምህርት እድል መስጠት
C. ዜጎች የቁጠባ ተቋማትን እንዲጠቀሙ ማስጠንቀቂያ መስጠት
D. የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን ከኢኮኖሚ ጋር አጣጥሞ ማስፋፋት

42. በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ኃላፊነትን በብቃት መወጣት ማለት ምን ማለት ነው?

A. ያለ ጥራት ስራን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ ነው።
B. እራስንና ቤተሰብን በሃላፊነት መጥቅምና ማስተዳደር።
C. ስራን በጥራት በመስራት ሀገርን መጥቀም ማለት ነው።
D. ከሌሎች ይልቅ ለራስ ደህንነት ጥንቃቄ ማድረግ።

2 11 2

43. የመንግሥት ተቋማት ላደረጉት ድርጊት ኃላፊነት መውሰዳቸው የሚኖረው ጥቅም፦

A. ዜጎች በመንግስት ላይ እምነት እንዲያሳድሩ ያስችላቸዋል።
B. ያላቸውን አቅም እንዳይጠቀመብት ያደርጋቸዋል።
C. ዜጎች የመንግሥትን ኃላፊዎች ለመተቸት ይረዳቸዋል።
D. ሰራተኞች በመንግስት ምስጋና እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

44. የተፈጥሮ ሀብቶችን በተመለከተ ትክክል የሆነውየትኛው ነው?የተፍጥሮ ሃብቶች፦

A. ሊታደሱ የማይችሉ ከሆኑ ያለገደብ መጠቀም ይቻላል።
B. የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መንግስት ብቻ ነው።
C. መጠበቅና መንከባከብ ሃላፊነትና ግደታው የግል ባለሃብቶች ነው።
D. የተፈጥሮ ሀብቶች የቱሪዝም ፍሰትን ይጨምራሉ።

45. ከሚከተሉት ውስጥ የጊዜ ጠቀሜታ በተመለከተ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. ጊዜ በስራ ላይ ጥሩ ነው።
B. ለሁሉም ሰው እኩል ጥቅም ይሰጣል።
C. ውጤታማ ስራ ለመስራት ቁልፍ መሳሪያ ነው።
D. ጊዜ ውስን ለሆኑ ሰዎች በትርፍ የተሰጠ ነው።

46. ጥሩ የሙያ ሥነምግባር መኖር ለጠንክራ የሥራ ባህል መዳበር ምን አስተዋፅኦ ያደርጋል?

A. ባህላዊ አስተሳሰብን ያጎለብታል
B. የስራ ተነሳሽነትን ይጨምራል
C. ያለአውቀት ስራ ለመስራት ያስችላል
D. አካላዊ ጥንካሬን በማጎልበት ድካም ይቀንሳል

47. ከሚከተሉት መከከል አንዱ የጥገኝነት አስከፊ ገፅታ ነው?

A. ከሰዎች ጋር አብሮ መኖርን እድንለምድ ያደርጋል
B. ውጤት ተኮር ሥራ ለማከናወን
C. የምንፈልገውን ሁሉ ከሰዎች እንዲንጠበቅ ያደርጋል
D. ከሰዎች ጋር ተካፍሉ መብላትን ያበረታታል

48. በራስ መተማመንን ለማጎልበት የሚያስችለው የትኛው ነው?

A. ደካማነንን ጠንቅቆ በማወቅ ማሻሻል
B. ለራስ የሚመቹ ሀሳቦችን ለይቶ ለመቅሰም
C. የሰዎችን ድክመት በመፈለግ መንቀፍ
D. መፅሃፍትን በማንበብ እውቀትን ማሳየት

49. የቁጠባ ባህል እንዳያድግ ምክንያት ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. ዘመናዊ የኋኋር ዘዴ መስፋፍት
B. የተጋነነ ውጭ የማውጣት ልምድ
C. የተመጠነ የቤተሰብ ቁጥር መኖር
D. በመጠነኛ ወጪ የሰርግ ስነስራዓትን ማክበር

50. ለአንድ ሀገር የቁጠባ ባህል መዳበር ጥቅሙ ምንዲን ነው?

A. አራስን ከማህበራዊ ግኑኝነት ለማቀብ።
B. የመንግስትን ገቢ ለመቆጣጠር።
C. የዜጎችን የኑሮ ደረጃ እኩል ለማድረግ።
D. የዜጎች የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲል ለማድረግ።

2 13 2

51. ለዲሞክራሲያዊ ሥራዓት ግንባታ አስፈላጊ **ያልሆነው** የትኛው ነው?

A. የመልካም አሥተዳደር መኖር
B. የኃለስብ የበላይነት
C. የሀግ የበላይነት
D. ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ

52. የሲቪክ ማህበራት ማለት ምን ማለት ነው?

A. ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ መኖር ማለት ነው።
B. የፖለቲካ ሥልጣን ለማግኘት የሚያደረግ ተግባርነው።
C. ትርፉ ለማግኘት የሚሰራ ተግባር ነው።
D. ማህበረሰቡን ካለክፍያ ማገልገል ማለት ነው።

53. ሰዎች ሳይንሳዊ እውቀታቸውን ለማዳበር ከሚጠቀሙበት መንገድ ውስጥ **የማይካተተው** የቱ ነው?

A. መገናኛ ብዙሀን
B. መደበኛ ያልሆነ ትምህርት
C. ባህላዊ የጥንቆላ ዘዴ
D. መደበኛ ትምህርት

54. ከሚከተሉት የመረጃ ማግኛ ዘዴዎች አንዱ ከሌሎች የተለየ ነው?

A. ጋዜጣ
B. ቴሌቭዥን
C. መፅሐፍት
D. በራሪ ወረቀቶች

56 ጎሳቀር አመለካከቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ሲፈጠሩ የሚችለው እንደትነው?

A. ዘመናዊ የእኗኗር ዘዴ መስፋፋት
B. ሳይንሳዊ አስተሳሰብ መስፋፋት
C. የጎሳቀር አስተሳሰብ በስፋት መኖር
D. ህብረተሰቡ ለሁሉም ስራዎች እኩል ክብር መስጠት

# 2 2



57. ከሚከተሉት መከለል የሴቶችን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. በምርጫ ውድድር ከወንዶች የተለየ መብት ማግኘት።
B. ገቢ በሚያስገኙ ስራዎችን የመስራት መብት አላቸው።
C. በኮታ የፖለቲካ ስልጣን የመያዝ መብት አላቸው።
D. በፍርድ ሂድት ከወንዶች የተለየ ልዩ ጥቅም ማግኘት።

58. ላይሰሩ መናር በሰዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት ምንድን ነው?

A. ከሰዎች ጋር ያላቸው መስተጋብር ይጨምራል
B. በቂ እረፍት እንዲያገኙና ጤናማ እንድሆኑ ያርጋቸዋል።
C. በራስ መተማመናቸው እንዲጨምር ያደርል።
D. የበታችነት ስሜት እንዳድርባቸው ያደርጋል።

59. የሴ አካባቢ ነዋሪዎች በአካባቢያቸው የሚታዩ ህገወጥ ተግባራትን ለፍትህ አካላት በማሳወቅ እርምጃ እንዲወሰድ እደረጉ።የነዋሪዎቹ ተግባር ምን ያመለክታል?

A. የሀግ የበላይነት መከበርን
B. የሚስጥር መጠበቅን
C. የፍትህ መጓደልን
D. የሰዎች መጎዳትን

60. ተማሪዎች የብሔር ብሔረሰቦችን በዓል በየዓመቱ ህዳር 29 በደማቅ ሁኔታ ያከብራሉ ። ይህ ሁኔታ የሚኖረው ጥቅም ምንዲን ነው?

A. ፍታታዊ ምርጫ እንዲኖር
B. የውጭ ግንኙነት እንዲጠናከር
C. የዜጎች ግንኙነት እንዲጠናከር
D. ተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደስልጣን እንዲመጡ

## የመጨረሻው ገፅ